የኢትዮጵያ
ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ)
ETHIOPIAN HUMAN RIGHTS COUNCIL (EHRCO)

# የሰብዓዊ መብቶችን አስመልክቶ ከኢሰመጉ የተላለፈ የአዲስ አመት ጥሪ

ጳጉሜ 05/2018 ዓ.ም

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ጉባዔ (ኢሰመጉ) በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅት አዋጅ ቁጥር 1113/2011 መሠረት ሀገር በቀል ድርጅት ሆኖ በ1984 ዓ.ም የተመሠረተና በምዝገባ ቁጥር 1146 ከ02/11/11 ዓ.ም ጀምሮ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለስልጣን ዳግም ተመዝግቦ በሕጋዊነት በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኝ መንግሥታዊ ያልሆነ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ድርጅት ነው። ኢሰመጉ የቋቋመበት ዋነኛ ዓላማው ዴሞክሪያሳዊ ሥርዓት ለማጎልበት፣ ለሕግ የበላይነት መስፈን ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ነው። በሥራውም ኢሰመጉ ላለፉት 34 ዓመታት በቆመላቸው አበይት ዓላማዎች ላይ በመመርኮዝ ሁለንተናዊ፣ ሀገራዊ ሕዝባዊ ተልዕኮ በመያዝ በነደፋቸው በርካታ የመራሐ-ግብር ተግባራት አማካኝነት ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ፤ የሕግ የበላይነት እና ሕጋዊ ሥርዓት እንዲሰፍን እና በኢትዮጵያ ዲሞክራያሲያዊ ሥርዓት እንዳይኖር እንቅፋት የሚሆኑ ጥሰቶችን በመመርመር፡ በመዘገብ እና በመወትወት የበኩሉን አስተዋጾያ በማበርከት ላይ ይገኛል።

ያሳለፍነው 2018 ዓ.ም በኢትዮጵያ የተለያዩ ኹነቶች የተከ ና ወ ኑ በ ት ና ዘርፈ ብዙ ችግሮች የተስተናገዱበት ዓመት ሲሆን በዓመቱ ከተከናወኑት አንኳር ተግባራት መካከል 7ኛው ሀገር አቀፍ ምርጫ በአብዛኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች በተያዘለት ጊዜ የተከናወነ መሆኑ፣ ሀገር አቀፍ ምክክሩ የአጀንዳ ማሰባሰብ ተግባሩን በማጠናቀቅ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተመካካሪዎችን በመምረጥ ከ4000 በላይ ከየአካባቢው የተውጣጡ ተወካዮች፣ ከተለያዩ ፖለቲካ ድርጅቶች፣ የክልል አስተዳዳሪዎችና ሌሎች መንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ከዲያስፖራ አካላትና ሌሎችም የተወከሉበት ምክክር መካሄዱ፤ እንዲሁም የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ ለማሳካት የሚያግዙ የህግ ማዕቀፎች ለማዘጋጀት እንስቃሴ የተደረገበት ዓመት በመሆኑ እነዚህ ጥረቶች የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታን ለማሻሻል የራሳቸውን አስተዎጾ ሊያደርጉ እንደሚችሉ እምነት የተወሰደበት ዓመት ነበር ።

2018 ዓ.ም ከላይ የተገለጹት በጎ ጅምሮች የታዩበት አመት ቢሆንም መጠነ ሰፊ የሆኑ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች የተፈጸሙበት ዓመት የነበረ ሲሆን ከእነዚህ ዘርፈ ብዙ ችግሮች መካከል በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች በሚንቀሳቀሱ ታጣቂዎች እና በመንግስት የጸጥታ አካላት መካከል በነበረው እና ለ ዓመታት በቀጠለው ግጭት በአማራና ኦሮሚያ ክልል በተለያዩ አካባቢዎች የበርካታ ሰዎች መገደል፣ የአካል ጉዳት፣ የንብረት ውድመት፣ ከቦታ ቦታ በነፃነት መንቀሳቀስ የተገደበበት፣ ዘረፋ፣ እገታና አስገድዶ መሰወር የተስፋፋበት፣ በተለይ በአማራ ክልል የህፃናት ትምህርት የቋረጠበት፣ በሴቶችና ህጻናት ላይ አስገድዶ የመደፈር ጥቃት የተስፋፋበት፣ በተለያዩ አካባቢዎች መፈናቀል በመበራከቱ በርካታ ህጻናት፣ ሴቶች፣ አካል ጉደተኞች፣ ወጣቶችና አረጋውያን ለከፍተኛ ችግር እየተዳረጉ የሚገኙበት፣ በመጠለያ ጣቢያ የሚገኙ ተፈናቃዮች የተለያዩ አስቸኳይና አንገብጋቢ የሆን ድጋፎች ጊዜውን ጠብቆ ስለማይቀርብ፣ መጠለያ ጣቢያዎች ከሸራ የተሰሩና እረጅም ጊዜ የሆናቸው በመሆኑ በተለይ በክረምቱ ለከፍተኛ ችግር እየተዳረጉ እና ዘላቂ መፍትሄ ያላገኙበት ዓመት ነበር። በግጭቱ ወቅት የተለያዩ ከባድ መሳሪያዎች ጥቅም ላይ የዋሉ በመሆኑ ንፁሀን የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ የግድያ፣ የአካል መጉደል እንዲሁም የንብረት ጉዳት አድርሰዋል።

በትግራይ ክልል የፕሪቶሪያውን ስምምነት ተከትሎ በአካባቢው በአንፃርዊነት ሰላምና መረጋጋት እየተመለሰ የነበር ቢሆንም ነገር ግን በስምምነቱ መሰረት ትጥቅ የማስፈታትና የማቋቋም ስራ ተግባራዊ ባለመደረጉ እና ተፈናቃዮች ወደ ቀያቸው መመለስ አለመቻላቸው፤

ህወሓት(TPLF) ጊዜያዊ አስተዳደሩን በማፍረስ የራሱን የአስተዳደር መዋቅር በመዘርጋቱ እና የቀድሞውን የክልል ምክር ቤት ወደ ስራ በመመለስ ከመሰረታዊ የሰብዓዊ መብት መርሆዎች ጋር የሚቃረኑ እና በኢፌዲሪ ህገ መንግስታዊ የተቀመጡ መሰረታዊ መብቶችን የሚጥሱ ውትድርናን አስገዳጅ የሚያደርጉ ህጎችን በማውጣት ወጣቶችን እና የአካባቢውን ነዋሪዎች ወደ ውትድርና ማሰልጠኛዎች ለማስገባት የሚያደርገውን እንቅስቃሴ እና በሀገር መከላከያ ኃይል በተለያየ ጊዜ ታጥቀው በሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ላይ የሚወሰደውን እርምጃዎች ተከትሎ  የአካባቢው ነዋሪዎች አካባቢው ወደ ዳግም ጦርነት ይገባል በሚል ስጋት  ማህበረሰቡ አካባቢውን ጥሎ ለመሰደድ የተገደደበት ዓመት ነበር።

በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ከመዋቅር ጥያቄዎች ጋር በተያያዘ በተለይ ዘይሴ ወረዳ ያለው ግጭት ተጠናክሮ የቀጠለበት እና  ለዜጎች ሞት፣ የአካል ጉዳት ፣ ንብረት መውደም እና ከመኖሪያ አካባቢያቸው መፈናቀል የደረሰበት፤ በጋምቤላ ክልል በተደጋጋሚ የጎሳ ግጭቶች የተስተዋሉበት እነዚህም ግጭቶች ዘርፈ ብዙ የሆነ የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን ያስከተሉበት፣ በአጠቃላይ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሕግ የበላይነትን የተፈታተኑ ችግሮች የታዩበትና ከህግ አግባብ ውጪ ጋዜጠኞች፣ አርቲስቶች፣ የተፎካካሪ ፓርቲ አባላት በዘፈቀደ የታሰሩበት ዓመት ነበር።

አዲሱ 2019 ዓ.ም በሀገሪቱ የቀጠሉት  የትጥቅ ግጭቶች በሰላምና በውይይት የሚፈታበት፣ ዜጎች ከቦታ ቦታ ያለምንም ስጋት የሚንቀሳቀሱበት፣ በተለያዩ አካባቢዎች በሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ቡድኖች የሚፈጸመው ማንነትን መሰረት ያደረገ ግድያና ማፈናቀል የሚቆምበት፣ በአደረጃጀት እና በመዋቅር ጥያቄዎች ምክንያት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ውስጥ የሚፈጸም ግድያና ማፈናቀል፣ ህገወጥ እስሮች ቀርተው ዘላቂ መፍትሔ የሚበጅበት እንዲሆን ለሁሉም አካላት ጥሪ እያቀረበን ከመኖሪያ አካባቢያቸው ተፈናቅለው የሚገኙ ዜጎች ዘላቂ መፍትሄ የሚያገኙበት፣ በመላ አገሪቱ የህግ የበላይነትን የሚፈታተኑ ችግሮች መፍትሔ በመስጠት የፍርድ ቤት ውሳኔዎች የሚከበሩበት ፣  በምክክር ኮሚሽን አማካኝነት የሚቀርቡ  ዋና ዋና እና መሰረታዊ የሀገሪቱንና የማህበረሰቡን ችግሮች ሊፈቱ የሚችሉ ምክረ ሃሳቦች ወደ ተግባር የሚለወጡበት፣ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲው ወደ ተግባር ለማስገባት የሚደረገው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ የሚቀጥልበት እና ወደ ተግባር የሚገባበት ዓመት ፣ መላው የአገሪቱ ህዝብም በመተሳሰብ፣ በሰላም፣ በአንድነትና በፍቅር ያሉትን ችግሮች በውይይትና በሰላም ለመፍታት የበኩሉን ድርሻ  እንዲወጣ ኢሰመጉ ጥሪ እያቀረበ አዲሱ ዓመት የህግ የበላይነት የሚሰፍንበት፣ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት የሚጎለብትበት እና ሰብዓዊ መብቶች የሚከበሩበት ዓመት እንዲሆን ኢሰመጉ መልካም ምኞቱን ይገልጻል።

## የኢሰመጉ ጥሪ፡

1. **ለኢትዮጵያ ፌዴራል መንግስት እና ለክልል መንግስታት**
    - **የሰላም ውይይት እንዲጀመር**:- በሀገሪቱ ያሉት የትጥቅ ግጭቶች በሰላም እና በውይይት እንዲፈቱ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሁሉን አቀፍ ግልፅ የሆነ የሰላም ውይይት በአስቸኳይ እንዲጀመር፤
    - **የዜጎችን ደህንነት እንዲያስከብሩ**:- በተለያዩ አካባቢዎች በሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ቡድኖች የሚፈፀሙ ግድያዎች ፣ ማፈናቀሎችንና እገታዎች በአስቸኳይ እንዲያስቆሙና ወንጀለኞችን ለህግ እንዲያቀርቡ፣ ዜጎች በሀገራቸው ውስጥ ያለምንም ስጋት በነፃነት የመንቀሳቀስ መብታቸውን እንዲያረጋግጡ፣
    - **ለጾታዊ ጥቃት ተጎጂዎች ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ፡-** በግጭቱ ወቅት ጾታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች እና ህጻናት ልዩ የህክምና፣ የስነ-ልቦና ድጋፍ እና ፍትህ የሚያገኙበት ስርዓት በአስቸኳይ እንዲዘረጋ።
2. **ለተፈናቃዮች ዘላቂ መፍትሄ እንዲመቻች፡** መንግስት **የአፍሪካ ህብረትን የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ስምምነት (Kampala Convention) ግዴታውን በመወጣት**፤ ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለው ለችግር የታዳረጉ ዜጎች ሁሉ ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲያገኙና በዘላቂነት የሚቋቋሙበት እና **ደህንነቱ የተጠበቀ፣ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ** እና ክብራቸውን የጠበቀ ዘላቂ መፍትሄ በአስቸኳይ እንዲያመቻች። **በሀገሪቱ ለሚንቀሳቀሱ የታጠቁ ቡድኖች**
    - **በንጹሃን ዜጐች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃትን እንዲያቆሙ**:- ፖለቲካዊ አላማን ለማሳካት በሚል በሲቪል ሰዎች ላይ የሚፈፀም ግድያ፣ ማፈናቀል፣ እገታን እና ሌሎች የሰብዓዊ መብት ጥሰቶችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲያቆሙ እና ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብትና የጦርነት ህጎችን በማክበር ለሰላማዊ ውይይት በራቸውን ክፍት እንዲያደርጉ፤ የሀገሪቱን ሰላም በበለጠ አደጋ ውስጥ ከሚከቱና የኢትዮጵያን ህልውና ከሚገዳደሩ ተግባራት በመቆጠብ የፖለቲካ ልዩነትን የዜጎችን ህይወት ዋጋ ከሚያስከፍሉ አካሄዶች በመታቀብና የፖለቲካ ልዩነትን በውይይት ለመፍታትና ሀገራዊ መፍትሄ ለመፈለግ የበኩላቸውን እንዲወጡ፤
3. **ለሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን እና የሽግግር ፍትህ አስተባባሪ ተቋማት**

   ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የተቋቋመበትን ዓላማ መሰረት በማድረግ ለኢትዮጵያ ይጠቅማሉ ተብለው የወጡ ምክረሀሳቦችን ለኢትዮጵያ ዘላቂ መፍትሄን እንጂ ተጨማሪ ችግርን እንደማይፈጥሩ ባረጋገጠ ሁኔታ በውይይቱ ተሳታፊ ከነበሩ የተለያዩ ወገኖች እየቀረቡ ያሉ ስጋቶችን ከግምት በማስገባት በአግባቡ በማጠናቀር መፍትሄ እንዲደረግባቸው ለሚመለከተው የመንግስት አካል እንዲያቀርብ

   የሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ሳይተገበር የተራዘመ ጊዜ የወሰደ በመሆኑ የሚያስፈልጉ ተቋማትን የማቋቋም ስራ በፍጥነት እንዲከናወን እና ወደ ተግባር እንዲለወጥ፤ አጠቃላይ ሂደቱ የተጎጅዎችን ፍትህ ማዕከል ባደረገ መልኩ እንዲከናወን።
4. **የሚዲያ ተቋማት**
    - ሀገርን ወደ ከፋ የደህንነት ስጋት ሊከቱ ከሚችሉ አሉታዊ ተግባራት በመታቀብ ዜጎች በመተማመን በሰላም ወጥተው የሚገቡበት ለሁሉም የምትመች ሀገር እንዲኖረን፤ የፖለቲካና የአስተሳሰብ ልዩነቶች ለሀገር ቀጣይነትና ለማህበረሰብ ደህንነት በሚጠቅም መልኩ በጠረጴዛ ዙሪያ በሚደረግ ውይይት መፍታት እንዲቻል የሚያደርጉና መንግስትም ሆነ ተቃዋሚ ሃይሎችን ወደ ድርድርና መነጋገር ሊያመጡ በሚችሉና አዎንታዊ ተጽዕኖ መፍጠር የሚችሉ ተግባራትን እንዲያከናውኑ፤
    - የሚዲያ ተቋማት የሙያ ስነ-ምግባራቸውን በመጠበቅ፤ በተለይም ብሔርንና ማንነትን መሰረት

ያደረጉ የጥላቻ ንግግሮችን እና ወደ ግጭት የሚያነሳሱ ቅስቀሳዎችን (Hate speech and incitement to violence) ከማሰራጨት በመቆጠብ፣ ለሰላም ግንባታና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር አዎንታዊ ሚና እንዲጫወቱ፤

5. **ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የሀይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች**
   - **ለሰላም የበኩላቸውን እዲወጡ፡-** በመተሳሰብ፣ በአንድነትና በፍቅር የሀገሪቱን ችግሮች በሰላማዊ ውይይት ለመፍታት በሚደረገው ጥረት ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉና የሰላም ባህልን እንዲያጎለብቱ ኢሰመጉ ጥሪውን ያቀርባል።

መልካም የኢትዮጵያ አዲስ ዓመት!
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ